# SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA

# የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ

# SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA

| | | |
|---|---|---|
| 2ki Diro Kiiro 18<br>Hawaasa, Wocawaaro 20, 2014 M.D | Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho<br>በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ፪ኛ ዓመት ቁጥር ፲፰<br>ሀዋሳ፣ መስከረም ፳ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም |



**Amado**

**Lallawu Kiiro 18/2014**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Jeefisiisaano Bissa Uurrisate, Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino Lallawa Kiiro 3/2012 Woyyeessate Fulino Lallawa … Qoola ….**

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፲፰/፳፻፲፬**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋም፣ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፫/፳፻፲፪ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ …… ገጽ ….**


## Lallawu Kiiro 18/2014

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Jeefisiisaano Bissa Uurrisate, Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino Lallawa Kiiro 3/2012 Woyyeessate Fulino Lallawa**

Qoqqowu mootimmata keeru, latishshu, farcotenna danchu gashshooti mixo jeefisiissanno jeefisaano uurrinshuwa konni albanni lallawu kiiro 3/2012 garinni uurrite loosanni nooti anfoonnita ikkitanna sai mittu diri yanna giddo noo xaphooma ha’rinshonni borreessantinoti kaajja loossa jawaatte suffanno gedenna laanfetenni leeltino hajubba yanna yannatenni woyyaabbanni

## አዋጅ ቁጥር ፲፰/፳፻፲፬

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋም፣ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፫/፳፻፲፪ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ**

የክልሉን መንግሥት የሠላም፣ የልማት፣ የፍትህና የመልካም አስተዳደር ዕቅዶችን የሚያስፈጽሙ አስፈጻሚ አካላት ከዚህ ቀደም በአዋጅ ቁጥር ፫/፳፻፲፪ መሰረት ተቋቁመው እየሰሩ እንደሚገኙ የሚታወቅ ሲሆን ባለፈው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በነበረው አጠቃላይ ሂደት የተመዘገቡ ጠንካራ ውጤቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉና በድክመት የተስተዋሉ ጉዳዮች


**Mittu Waagi ….**
**ያንዱዋጋ**

AFFINI GAAZEEXI P.S.K …..
አፍኒ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. …..
Web address: www.affinigazet.gov.et

hadhanno xaphooma amuraate sirsa hasiissannota ikkitinohura;

Daga mootimmate uytinota xaphooma sokko woyyawino garinni jeefisate dandiisiisanno garinni mootimmate uurrinshubba tantano gobboomunna qoqqowu deerrinni heedhanno soorro kaima assatenni hasishshu garinni yanna yannatenni woyyeessanna uurrinshubba dagoomaho uytanno owaantubba dhuku fajji bikkinni tuqqinnota, hanqaffannota, waaxotenni loosantannotanna jiro garunni horonsi'ra hedote worino garinni ikkansa buuxisa hasiissannohura;

Konni kaiminni qoqqowunnita jeefisiisanno bissa tantano, biilloonyenna loosu qeecha boodu garinni woyyeessanno seera fushsha hasiisinohura;

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Amaale mini qoqqowu Bayriidi Seeri quwa 48 cinaancho quwa 3 fidale (a) iima uynoonnisi biilloonyi garinni aaninoha lallawino.

1. **Harancho Su'ma**

   Kuni lallawi "Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Jeefisiisaano Bissa Uurrisate, Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino Lallawa Kiiro 3/2012 Woyyeessate Fulino Lallawa Kiiro 18/2014" yaamame maqisamara dandaanno.

2. **Woyyeesso**

   Qoqqowinita Jeefisiisaano Bissa Uurrisate, Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino

በየወቅቱ እየተስተካከሉ የሚሄዱበትን አጠቃላይ ሥርዓት መከተል አስፈላጊ በመሆኑ፣

ሕዝቡ ለመንግሥት የሰጠውን አጠቃላይ ተልዕኮ በተሻለ ሁኔታ ለመፈጸም እንዲቻል የመንግሥት ተቋማት አደረጃጀትን በሀገር አቀፍና በክልል ደረጃ የሚኖሩ ለውጦችን መነሻ በማድረግ እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው መከለስ እና ተቋማቱ ለሕብረተሰቡ የሚሰጧቸው አገልግሎቶች አቅም በፈቀደ መጠን ተደራሽ፣ አካታች፣ በቅንጅት የሚፈጸሙ እና ሀብትን በአግባቡ መጠቀምን ታሳቢ ያደረጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ስለሚገባ፤

ከዚህም አንጻር የክልሉን አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን በተወሰነ መልኩ የሚያሻሽል የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት በማስፈለጉ፣

የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፰ ንዑስ አንቀጽ ፫ ፊደል ተራ (ሀ) ላይ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የሚከተለውን አውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ለማቋቋም፣ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፫/፳፻፲፪ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፰/፳፻፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ማሻሻያ**

   የክልሉን አስፈጻሚ አካላት ለማቋቋም፣

Lallawu Kiiro 3/2012 (Konni gedensanni “albi lallawi” yinanni woshshinannihu) iima konni woroonni noore konni lallawinni woyyeesinoonni.

1. Albi lallawi quwa 9 rigidame konni woroonni noohunni riqiwamino.

**“ 9. Jeefisiisaanote bisubba uurronna hundaanchimma**

Pirezidaantichaho galtannorinna qoqqowu jeefisiisaanote amaale minira miilla ikkitinori konni woroonni dirroonniri jeefisiisaano bisubba seeru mannimma noonsare ikkite konni lallawinni uurritino.

1. Keerunna Gal’abbote Biiro
2. Irshunna Kalaqamu Jiro Latishshi Biiro
3. Fayyimmate Biiro
4. Rosu Biiro
5. Faynaansete Biiro
6. Xaphoomu Seeru Allaalsha
7. Eote Biilloonye
8. Doogote Latishshinna Hodhishshu Biiro
9. Daddalunna Industirete Latishshi Biiro
10. Quchumu Latishshinna

ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር ፫/፳፻፲፪ (ከዚህ በኋላ “ነባሩ አዋጅ” እየተባለ በሚጠራው) ላይ ከዚህ በታች የተመለከቱ ማሻሻያዎች በዚህ አዋጅ ተደርጓል፡፡

1. የነባሩ አዋጅ አንቀጽ 9 ተሰርዞ ከዚህ በታች ባለው ተተክቷል፡፡

**“ 9. የአስፈጻሚ አካላት መቋቋምና ተጠሪነት**

ለርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪ እና የመስተዳድር ምክር ቤት አባል የሆኑ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አስፈጻሚ አካላት የሕግ ሰውነት ያላቸው ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

1. የሠላምና ፀጥታ ቢሮ
2. የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ
3. የጤና ቢሮ
4. የትምህርት ቢሮ
5. ፋይናንስ ቢሮ
6. ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ
7. የገቢዎች ባለሥልጣን
8. የመንገድ ልማትና ትራንስፖርት ቢሮ
9. የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ
10. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን

Konistirakishiinete Biiro

11. Way, Shiilotenna Inerjete Biiro
12. Meentu, Wedellunna Dagoomitte Hajubba Biiro
13. Wogate, Turizimetenna Ispoortete Biiro
14. Loosu, Dandootenna Interprayizete Latishshi Biiro
15. Dagitte Owaantenna Mannu Jiro Latishshi Biiro
16. Pilaanetenna Latishshu Biiro
17. Saadate Jiro Latishshi Biiro ”

2. Albi lallawi quwa 10 rigidame konni woroonni noohunni riqiwamino.

**“ 10. Hundaano Jeefisiisaano Bissa Uurronna Hundaanchimma**

1. Pirezidaantichu Borro Minira hundaano ikkitinonna konni woroonni dirroonniri jeefisiisaano bissa seeru mannimma noonsare ikkite konni lallawinni uurritino.

a) Pirees Sekireteriyate

b)Diyaspooru Latishshu Beeqqaanchimma Qineesso Borro Mine

c)Dubbu, Qarqaru Agarooshshinna

ቢሮ

11.የውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ
12. የሴቶች፣ ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ቢሮ
13. የባህል፣ ቱርዝምና ስፖርት ቢሮ
14. የሥራ፣ የክህሎትና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ
15.የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ
16. የፕላንና ልማት ቢሮ
17. የእንስሳት ሀብት ልማት ቢሮ ”

2. የነባሩ አዋጅ አንቀጽ 10 ተሰርዞ ከዚህ በታች ባለው ተተክቷል፡፡

**“10. የተጠሪ አስፈጻሚ አካላት መቋቋምና ተጠሪነት**

1. ለርዕስ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት ተጠሪ የሆኑና ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አስፈጻሚ አካላት የሕግ ሰውነት ያላቸው ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

ሀ) የፕሬስ ሴክሬታሪያት

ለ) የዲያስፖራ በልማት ተሳትፎ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት

ሐ) የደን፣ የአካባቢ ጥበቃና የአየር

Diilallote Gade Soorro Biilloonye

2. Keerunna Gal'abbote Biirora hundaano ikkitinonna konni woroonni dirroonniri jeefisiisaano bissa seeru mannimma noonsare ikkite konni lallawinni uurritino:

a) Poolisete Komishiine

b)Hasiisaancho Ikkito Borreessishshi Ejense

c) Danote Yaaddo Loosi Massago Komishiine

d) Milishu Borro Mine

3. Irshunna Kalaqamu Jiro Latishshi Biirora hundaano ikkitinonna konni woroonni dirroonniri jeefisiisaano bissa seeru mannimma noonsare ikkite konni lallawinni uurritino:

a) Bunu, Laalotenna Qimammate Biilloonye

b) Giwirinnu Xiinxallo Institiyute

c) Mittimmate Loosi Maamarra tantanonna Halashsho Ejense

d)Giwirinnu Giwaate Isilanchimma Buuxonna Kuwaarantiinete Biilloonye

4. Fayyimmate Biirora hundaano ikkitinonna konni woroonni dirroonniri jeefisiisaano bissa seeru

ንብረት ለውጥ ባለሥልጣን

2. ለሠላምና ፀጥታ ቢሮ ተጠሪ የሆኑና ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አስፈጻሚ አካላት የሕግ ሰውነት ያላቸው ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

ሀ) ፖሊስ ኮሚሽን

ለ) የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ

ሐ) የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን

መ) የሚሊሻ ጽሕፈት ቤት

3. ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ተጠሪ የሆኑና ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አስፈጻሚ አካላት የሕግ ሰውነት ያላቸው ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

ሀ) የቡና፣ ፍራፍሬና ቅመማ ቅመም ባለሥልጣን

ለ) የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

ሐ) የሕብረት ሥራ ማኀበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ኤጀንሲ

መ) የግብርና ግብዓቶች ጥራት ቁጥጥርና ኳራንቲን ባለሥልጣን

4. ለጤና ቢሮ ተጠሪ የሆኑና ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አስፈጻሚ አካላት

mannimma noonsare ikkite konni lallawinni uurritino:

a) Dagoomu Fayyimmate Institiyute

b) Fayyimmatenna Fayyimate Owaantera Hasiisano Udiinichi Islanchimma Qorqorate Biilloonye

c) Mootimmate Fayyimmate Sayinse Kolleejuwa

5. Mootimmate Rosiisaanote Rosi Kollejuwa Rosu Biirora hundaanonna seeru mannimma noonsa jeefisiisaano bissa ikkite konni lallawinni uurritino.

6. Mootimmate Latishshu Uurrinshuwa Qorqorshi Biilloonyi Faynaansete Biirora hundaanchonna seeru mannimma noosi jeefisiisaancho biso ikke konni lallawinni uurrino.

7. Xaphoomu Seeru Allaalshira hundaano ikkitinonna konni woroonni dirroonniri jeefisiisaano bissa seeru mannimma noonsare ikkite konni lallawinni uurritino:

a) Seeru Seejjo Minna Komishiine

b) Taakisete Kado Komishiine

8. Dooggate Biilloonyi Doogote

የሕግ ሰውነት ያላቸው ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

ሀ)የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት

ለ)የጤናና ጤና ነክ አገልግሎቶችና ግብዓቶች ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን

ሐ) የመንግሥት ጤና ሳይንስ ኮሌጆች

5. የመንግሥት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ለትምህርት ቢሮ ተጠሪና የሕግ ሰውነት ያላቸው አስፈጻሚ አካላት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

6. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ለፋይናንስ ቢሮ ተጠሪና የሕግ ሰውነት ያለው አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

7. ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ተጠሪ የሆኑና ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አስፈጻሚ አካላት የሕግ ሰውነት ያላቸው ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

ሀ) የማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን

ለ) የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን

8. የመንገዶች ባለሥልጣን ለመንገድ ልማትና ትራንስፖርት ቢሮ

Latishshinna Hodhishshi Biirora hundaanchonna seeru mannimma noosi jeefisiisaancho biso ikke konni lallawinni uurrino.

9. Investimentete Komishiine Daddalunna Industirete Biirora hundaanchonna seeru mannimma noose jeefisiisaancho biso ikkete konni lallawinni uurritino.

10. Quchumu Latishshinna Konistiraakishiinete Biirora hundaano ikkitinonna konni woroonni dirroonniri jeefisiisaano bissa seeru mannimma noonsare ikkite konni lallawinni uurritino:

a) Konistiraakshiinete Biilloonye

b) Quchummate Pilaane Institiyute

11. Way, Shiilotenna Inerjete Biirora hundaano ikkitinonna konni woroonni dirroonniri jeefisiisaano bissa seeru mannimma noonsare ikkite konni lallawinni uurritino:

a) Gorsu Latishshi Ejense

b) Shiilotenna Inerjete Ejense

12. Wogate, Turizimetenna Ispoortete Biirora hundaano ikkitinonna konni woroonni dirroonniri jeefisiisaano bissa seeru mannimma noonsare ikkite konni lallawinni uurrino:

a) Sidaamu Afii Xiinxallo

ተጠሪና የሕግ ሰውነት ያለው አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

9. የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ለንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ተጠሪና የሕግ ሰውነት ያለው አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

10. ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ተጠሪ የሆኑና ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አስፈጻሚ አካላት የሕግ ሰውነት ያላቸው ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

ሀ) የኮንስትራክሽን ባለሥልጣን

ለ) የከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት

11. ለውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ ተጠሪ የሆኑና ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አስፈጻሚ አካላት የሕግ ሰውነት ያላቸው ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

ሀ) የመስኖ ልማት ኤጀንሲ

ለ) የማዕድንና ኢነርጂ ኤጀንሲ

12. ለባህል፣ ቱርዝምና ስፖርት ቢሮ ተጠሪ የሆኑና ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አስፈጻሚ አካላት የሕግ ሰውነት ያላቸው ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

ሀ)የሲዳሙ አፎ ጥናት

Institiyute

b) Ispoortete Komishiine

13. Loosu, Dandootenna Interprayizete Latishshi Biirora hundaano ikkitinonna konni woroonni dirroonniri jeefisiisaano bissa seeru mannimma noonsare ikkite konni lallawinni uurrino:

a) Ogimmate Dandoo Buuxo Ejense

b) Sayinsetenna Tekinolojete Ejense

c) Mootimmate Tekiniketenna Ogimmate Qajeelshi Kolleejuwa

14. Konni quwi cinaanchu quwi 1-13 geeshsha worroonni hundaano uurrinshubba giddonni hundaanchimmatenna biilloonyunna loosu qeechi soorro assinoonnikkiri hattono biilloonyunna loosu qeechi soorro assinikkinni hundaanchimate soorro calla assinoonni uurrinshubba balaxe fulino seerinni uynonninsa biilloonyinna loosu qeechi garinni loossannoha ikkanno.

15. Konni quwi cinaanchu quwi 1-13 geeshsha worroonni hundaano uurrinshubba giddonni

ኢንስቲትዩት

ለ) ስፖርት ኮሚሽን

13. ለሥራ፣ የክህሎትና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ ተጠሪ የሆኑና ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አስፈጻሚ አካላት የሕግ ሰውነት ያላቸው ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

ሀ) የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ኤጀንሲ

ለ) የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ

ሐ)የመንግሥት የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኮሌጆች

14. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 – 13 ከተዘረዘሩት ተጠሪ ተቋማት መካከል የተጠሪነት፣ የሥልጣንና ተግባር ለውጥ ያልተደረገባቸው እንዲሁም የሥልጣንና ተግባር ለውጥ ሳይደረግ የተጠሪነት ለውጥ ብቻ የተደረገባቸው ተቋማት አስቀድሞ በወጣው ሕግ በተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር መሰረት የሚሰሩ ይሆናሉ፡፡

15. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 – 13 ከተዘረዘሩት ተጠሪ ተቋማት መካከል የተጠሪነት፣ የሥልጣንና ተግባር ለውጥ

hundaanchimmate, biilloonyunna loosu qeechi soorro assineenna uurritino jeefisiisaano uurrinshuwa tantano, biilloonyunna loosu qeechi qoqqowu jeefisiisaanote amaale mini fushshanno wodhonni murranniha ikkanno.

3. Albi lallawi quwa 14 konni woroonni noo garinni woyyaawino.

**A)** Albi lallawi quwa 14 fidale (b) iima rigidante konni woroonni nootenni riqiwantino.

“B) Irshunna Kalaqamu Jiro Latishshi Biiro

1. Qoqqowunnita irshunna kalaqamu jiro, irshu laalchonna eote dikki’ro, irshu eo shiqisho lainohunni polisete hedo shiqishshanno; qixxeessitanno; gumulsiishshu aanti-gedeni istiraateeje fushshitanno; kaajjirono loosu aana hosiissanno.
2. Baadiyyete sagalete waastinni qarrira reqeccishantino qarqarranna dagoomu biso badanno; kora xiinxallanno; irkisanno; sagalete waastinni pirogiraamma massagganno; handaaraho loossannore

ተደርጎባቸው የተቋቋሙ አስፈጻሚ ተቋማት አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር የመስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡ ”

3. የነባሩ አዋጅ አንቀጽ 14 ከዚህ በታች እንደተመለከተው ተሻሽሏል፡፡

**ሀ)** በነባሩ አዋጅ አንቀጽ 14 ፊደል ተራ (ለ) ተሰርዞ በሚከተለው ተተክቷል፡፡

“ለ) የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ

1. የክልሉን የእርሻና፣ የተፈጥሮ ሃብት፣ የእርሻ ምርትና ግብዓት ግብይት፣ የእርሻ ግብዓት አቅርቦትን በሚመለከት የፖሊሲ ሃሳቦችን ያቀርባል፣ ያዘጋጃል፣ የአፈፃፀም ቅደም ተከተል ስትራቴጂ ያወጣል፣ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
2. በገጠር ለምግብ ዋስትና ችግር የተጋለጡ አካባቢዎችንና የኅብረተሰብ ክፍሎችን ይለያል፣ መንስኤውን ያጠናል፣ ይደግፋል፣ የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞች ይመራል፣ በዘርፉ የሚሠሩ

qeechi-gutamaano bisubba buusansiissanno.

3. Baatto loosidhe galtinorira aamantannota irshunna kalaqamu jiro ekisteenshiinete owaante hala'litara loossanno; jawaachishshanno.
4. Garimma noonsa bisubba ledo buusamatenni baatto loosidhe galtinori irshunna kalaqamu jiro loosonsa woyyeesi'rate hasiissannonsata liqoote injo afidhanno gara injeessitano.
5. Irshunna kalaqamu jiro investimentera bobbakkino dureeyyera irko uytanno.
6. Irshu latishshi aana hekko kalaqara dandaannore ha'runsitanno; balxi-qorophotenna balaxi-qixaawote amuraate diriirsitanno.
7. Qoqqowoho daafotenna togoori gidu dhibbanna gidimale gargaratenna qorqorate hasiissanno qaafo adhitanno.
8. Gorsu latishshi loosi hala'lanno gede jeefisiisate hayyo qixxeessitanno; jeefisiisanno.
9. Qoqqowoho hala'litanno paakeejuwa loosu aana hosiisate hasiissannota irshu

ባለድርሻ አካላትን ያስተባብራል፡፡

3. ለአርሶ አደሩ የሚሰጡ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ይሰራል፣ ያበረታታል፡፡
4. አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር አርሶ አደሩ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሥራውን ለማሻሻል የሚያስፈልገውን የብድር አቅርቦት የሚያገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
5. በእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ ባለሃብቶች ድጋፍ ይሰጣል፡፡
6. በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን ይከታተላል፣ የቅድመ ማስጠንቀቂያና ቅድመ ዝግጁነት ስርዓት ይዘረጋል፡፡
7. በክልሉ የወረረሽኝና ተዛማች አዝርዕት በሽታዎችና ፀረ-ሰብል ለመከላከልና ለመቆጣጠር አስፈላጊ እርምጃ ይወስዳል፡፡
8. የመስኖ ልማት ስራ እንዲስፋፋ የአፈፃፀም ስልቶችን ያዘጋጃል፣ ያስፈጽማል፡፡

eora ikkitannorenna liqoo hasi'nanni silanchimmanni, bikkinninna yannanni baatto loosidhe galtinorira shiqishshanno; irshu laalchi baadinna baara widi dikko safo assi'rinoha ikkanno gede injeessitanno; ha'runsitanno; illaallissanno.

10. Irshu laalchimma lossate kaa'litanno xiinxallo ha'rinsanni gede assitanno; loosu aana hosansa ha'runsitanno.
11. Qoqqowunniti kalaqamu jiro lattanno gede, qorowantanno gedenna horoonshise woyyaawanno gede irkissanno polisenna istiraateeje qixxeessitanno; kaajjituro loosu aana hosiissanno; loosu aana hosansa garan ha'runsitanno; illaallissanno.
12. Garanna taalo ikkinohu baattote horoonshinna gashshooti hee'rara dandiissitanno polisena istiraateeje qixxeessitanno; kaajjituro loosu aana hosiissanno; loosu aana hosi gara ha'runsitanno; illaallissanno.
13. Giwirinnu xiinxallo qeechi-gutamaano bisubba

9. በክልሉ የሚስፋፉ ፓኬጆች ለመተግበር የሚያስፈልጉ የእርሻ ግብአቶችና ብድሮች በሚፈለገው ጥራት፣ መጠንና ጊዜ ለአርሶ አደሩ ያቀርባል፤ የእርሻ ምርት የውስጥና ውጪ አገር ገበያ መሰረት ያደረገ እንዲሆን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
10. የእርሻ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚረዱ ጥናቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፡፡
11. የክልሉ የተፈጥሮ ሃብት እንዲለማ፣ እንዲታቀብና አጠቃቀሙ እንዲሻሻል የሚያግዝ ፖሊሲና ስትራተጂ ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅ በተግባር ያውላል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
12. ፍትሃዊ የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር እንዲኖር የሚያስችል ፖሊሲ፣ ስትራተጂ፣ ያዘጋጃል፡፡ ሲፀድቅ ተግባር ላይ ያውላል፣ ስለተግባራዊነቱ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
13. ግብርና ምርምር ባለድርሻ አካላት በቅንጅትና በትብብር የሚሰሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

waaxantenna buusante loossanno amuraate diriirsitanno.

14. Meentonna wedella safo assidhinota irshunna kalaqamu jiro paakeeje polisete deerrinni qixxeessitanno; kaajjituro loosu aana hosanna gara ha'runsitanno.
15. Dikko shiqqannore eo ikkitanno bushshu shiilonna irshu guma labbinori isilanchimma buuxxanno; ha'runsitanno; illaallissanno.
16. Hexxo jeefa gansiissannota wole assootubbano wonshitanno."

**B)** Albi lallawi quwa 14 fidale (E) rigidante konni woroonni nootenni riqiwantino.

"E) Fayinaansete Biiro

1. Qoqqowu mootimma baajete qixxeessitanno, fajjinonni baajete kaiminni baattanno, baajetete jeefishsha gashshitanno, keentanno, qorqortanno;
2. Qoqqowu mootimma baajeette, shallago, baatooshshe, giddoydi odiite amanyoote xintitanno,

14. ሴቶችና ወጣቶችን መሰረት ያደረጉ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ፓኬጅ በፖሊሲ ደረጃ ይቀርፃል፣ ሲፀድቁ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡
15. ወደ ገበያ የሚቀርቡ ግብአቶች እንደ ማዳበሪያና የእርሻ ውጤቶች ጥራት ያረጋግጣል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
16. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡"

**ለ)** በነባሩ አዋጅ አንቀጽ 14 ፊደል ተራ (ሠ) ተሰርዞ በሚከተለው ተተክቷል፡፡

"ሠ) የፋይናንስ ቢሮ

1. የክልል መንግሥት በጀት ያዘጋጃል፣ በተፈቀደው በጀት መሰረት ክፍያ ይፈፅማል፣ የበጀቱን አፈፃፀም ያስተዳድራል፣ ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል፡፡
2. የክልሉ መንግስትን የበጀት፣ የሂሳብ፣ የክፍያና፣ የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ይዘረጋል፣ በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፡፡
3. ከመንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚገኝ

loosu aana hosase ha’runsitanno;

3. Mootimmaanonna mootimmaaweelo uurrinshuwanni afantanno kaa’lonna liqoo buusansiisatenni qoqqowu latishshu baajeette mixo ledo qinaawe loosu aana hossara injeessitanno; qineessitanno; ha’runsitanno.
4. Qoqqowoho leeltannota dagoomaanchonna miinjitte mitiimma shotisate sumiimmete kaiminni dagganno kaa’lo loosu aana hossara irko assitanno; buusansiissanno; gashshitanno; lexxote kaa’lo afi’rate babbaxxitino pirojektuwa qixxeessatenninna qixxeessiisatenni kaa’lo assitanno uurrinshuwara shiqishshanno.
5. Miinjunna dagoomu latishshi handaarira bobbakkinore mootimmaanonna mootimmaaweelo uurrinshuwa looso la’annonsari ledo halamatenni buusansiissanno; illaallissanno.
6. Fajjaameeyye uurrinshuwanna maammarra pirogiraammatanna pirojektuwata ikkadimmate keeno assitanno; loosu

እርዳታና ብድር በማስተባበር ከክልሉ የልማት በጀት ዕቅድ ተጣጥሞ በስራ እንዲውል ያመቻቻል፣ ያቀናጃል፣ ይከታተላል፡፡

4. በክልሉ የሚታዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለማቃለል በስምምነት መሰረት የሚመጡ እርዳታዎች በስራ ላይ እንዲውሉ ድጋፍ ይሰጣል፣ ያስተባብራል፣ ያስተዳድራል፣ ተጨማሪ እርዳታዎች ለማግኘች የተለያዩ ፕሮጀክቶች በመቅረፅና እንዲቀረፅ በማድረግ እርዳታ ለሚሰጡ ድርጅቶች ያቀርባል፡፡
5. በኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ዘርፍ የተሰማሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ስራ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፡፡
6. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኀበራት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን የብቃት ምዘና ያደርጋል፤ የሥራ ውል ይፈራረማል፤ ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤ ይገመግማል፡፡
7. የክልሉ የመንግስት አካላት በክልሉ መንግስት የፋይናንስ ፖሊሲና ሕጎች መሰረት

sheemaate malaatisantanno; buusansiissanno; ha’runsitanno; keentanno.

7. Qoqqowunniti mootimmate bisubba qoqqowu mootimma womaashshu polisenna seeri garinni loosansa illaallissanno.
8. Qoqqowu mootimmaha eo gamba assinanni woraqata attansiissanno; tuqissanno; ha’runsitanno; qorqortanno.
9. Qoqqowu mootimma fiisikaaletenna womaashshu loosi guunte leellishannoha tittirshu xawishsha pirezidaantichaho, qoqqowu jeefisiisaanote amaale miniranna seerunni biilloonye uynoonninsa bisubbara yannatenni shiqishshanno.
10. Qoqqowu mootimma shalagote amadooshshi amuraate qixxeessitanno; loosu aana hosanna gede irkissanno; giddo qorqorshi amuraate diriirsitanno.
11. Qoqqowu mootimma babbaxxitino buenni afidhannota liqootenna kaa’lote sumiimme qoqqowu mootimma su’minni malaatissanno; liqoote massagooshshe gashshanno.
12. Qoqqowu mootimma aksiyonna tareessantannonna

መስራታቸውን ይቆጣጠራል፡፡

8. የክልሉን መንግስት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ያሳትማል፣ ያሰራጫል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
9. የክልሉ መንግስት የፊስካል እና የፋይናንስ የስራ አፈፃፀም የሚያሳይ ዝርዝር መግለጫ ለርዕሰ መስተዳድሩ፣ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትና በሕግ ስልጣን ለተሰጣቸው አካላት በወቅቱ ያቀርባል፡፡
10. የክልሉ መንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ይነድፋል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ይደግፋል የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
11. የክልሉ መንግስት ከተለያየ ምንጭ የሚያገኘውን የብድርና ዕርዳታ ስምምነት በክልሉ መንግስት ስም ይፈርማል፣ ብድሩን ያስተዳድራል፡፡
12. የክልሉ መንግስት አክሲዮኖች፣ የሚተላለፉና የማይተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችና ሌሎች ተመሳሳይ የገንዘብ ሰነዶች ይይዛል፣ ይጠብቃል፡፡
13. በክልሉ መንግስት የተቋቋሙ የልማት ድርጅቶችን አጠቃላይ እንቅስቃሴን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ይቆጣጠራል፡፡

tareessantannokkiti woxu sanadda amaddanno; agartanno.

13. Qoqqowu mootimmanni uurritinota latishshu uurrinshuwata xaphooma millimmo ha’runsitanno; irkissanno; illaallissanno.
14. Qoqqowu mootimmaha jajju gashshootenna hidhote amuraate diriirsitanno; gumulaanchimma illaallissanno; irkissanno; seeraancho taashshote qaafo adhitanno; adhinanni gedeno assitanno.
15. Gongo’maasine, jajjabba maashinna, jajjabba hiro-hidho kamalte hirtanno; kayissanno; kaysate ledo amadantino loossa wonshitanno; hasiisi garinni riqiwooshshe uytanno.
16. Mootimmate hiro-hidhora ayirritanno lawashshimma leellishshanno shiqishaanora qorophishsha uytanno; murantinonna murantinokki yanna geeshsha shiqishaanchimmatenni ittissanno.
17. Gumulantino hidho lallawunna biddissu garinni gumulamansanna gara ikkinohu jajju gashsho amuraati diriirsamasi buuxi’rate hidhotenna jajju gashshooti

14.የክልሉ መንግስት የንብረት አስተዳደር እና የግዢ ስርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል፣ ይደግፋል፣ህጋዊ ማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡
15.ተሽከርካሪዎች፣ ትላልቅ ማሽኖች፣ ትላልቅ ግዥዎች በጥቅል ይገዛል፣ ያስወግዳል፣ ከማስወገድ ጋር የተያያዙ ስራዎች ይፈፅማል፣ እንደአስፈላጊነቱ ውክልና ይሰጣል፡፡
16.በመንግስት ግዥ አፈፃፀም ከባድ ቸልተኝነት የሚያሳዩ አቅራቢዎች ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፣ ለተወሰነና ላልተወሰነ ጊዜ ከአቅራቢነት ያግዳል፡፡
17.የሚፈፀሙ ግዥዎች በአዋጅና መመሪያ መሰረት መፈፀማቸውንና ትክክለኛ የንብረት አስተዳደር ስርዓት መዘርጋቱን ለማረጋገጥ የግዥና የንብረት አስተዳደር ኦዲት ያደርጋል፡፡
18.አስፈፃሚ አካላት ከመንግሥታዊ ኢንተርፕራይዝ በቀጥታ ግዥ እንዲፈፀሙ ይፈቅዳል፡፡
19. የመንግሥት ተሽከርካሪ

qorqorsha assitanno.

18. Jeefisiisaano bisubba mootimmaano interprayzenni dhaaddo hidho gumultara fajjitanno.
19. Mootimmate gongo'maasine amadooshshinna horoonshi amuraate ha'runsinoha ikkanno gede assitanno.
20. Hexxo jeefa gansiisate kaa'litannota wole assootubba wonshitanno."

**C)** Albi lallawi quwa 14 fidale (I) rigidante konni woroonni nootenni riqiwantino.

"I) Daddalunna Industirete Biiro

1. Daddalunna investimente hala'litanno gede injaaduri kalaqamanno assitanno.
2. Qoqqowu giddo daddalo halashshatenna kaajjishate lifixa dikki'rote amuraatenna gara ikkitinoti daddalu loosi ha'rinsho hala'litanno gede assitanno.
3. Garimmaanchu seeri garinni daddalu borreessammishshanna fajjootu owaante uytanno; illaallissanno; hutanno; daddalu borreessamaasincho qixxeessitanno.
4. Seerunni addi garinni wolu

አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት የተከተለ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

20. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡"

**ሐ)** በነባሩ አዋጅ አንቀጽ 14 ፊደል ተራ (ቀ) ተሰርዞ በሚከተለው ተተክቷል፡፡

"ቀ) የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ

1. ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፡፡
2. በክልሉ ውስጥ ንግድን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ቀልጣፋ የግብይት ሥርዓትና ተገቢ የንግድ አሠራር እንዲሰፍን ያደርጋል፡፡
3. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፣ የንግድ መዝገብ ያደራጃል፡፡
4. በሕግ በልዮ ሁኔታ ለሌላ አስፈፃሚ አካል የተሰጠው እንደተጠበቀ ሆኖ ህገ-ወጥ የግብርና ምርቶች ዝውውር ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ በህግ አግባብ እርምጃ ይወስዳል፡፡
5. በሕግ በልዩ ሁኔታ ለሌላ

jeefisiisaanote bisira aamammohu noo gedeenni hee’reenna seerimale giwirinnu laalchi doyisso illaallissanno; ha’runsitanno; seerunni gara qaafo adhitanno.

5. Seerunni addi garinni wolu murrate bisira aamammohu noo gedeenni hee’reenna dikki’rote amuraate aliidimmatenni massagganno; ha’runsitanno; irko assanno.
6. Garimale daddalu assoote gargarate dandiissannoha wo’millaancho amuraate diriirsitanno; daddalu seeri ayirrisamasi buuxxanno; guuntensa/gumulaanchimmansa ha’runsitanno.
7. Qoqqowoho noohu dikkote quraanyo amuraati shiqishonna hasatto mereersinoha ikkanno gede hayyo maltanno; illaallissanno.
8. Qoqqowu giddo laashshinanni laalchi gobbate babbaxxino qarqariranna baara wido afantanno dikkote doorshuwara shiqannota dikkote quraanyo kalaqate loossanno.
9. Dikkote foonqe leeltanno udiinninna owaante ragaanni qoqqowu mootimma doorammo garinni foonqe wonshitannota

አስፈፃሚ አካል የተሰጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የግብይትን ሥርዓት በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

6. ተገቢ ያልሆነ የንግድ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችል የተሟላ ሥርዓት ይዘረጋል፣ የንግድ ሕጎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፡፡
7. በክልሉ ያለው የገበያ ትስስር ሥርዓት አቅርቦትንና ፍላጎትን ያማከለ እንዲሆን ስልቶችን ይቀይሳል፣ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
8. በክልሉ ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች እና ከሀገር ውጭ በሚገኙ የገበያ አማራጮች ላይ የሚቀርቡበትን የገበያ ትስስር ለመፍጠር ይሰራል፡፡
9. የገበያ ክፍተት በሚታይባቸው የዕቃ እና አገልግሎት ዘርፎች የክልሉ መንግስት በተመረጠ አኳሄን ክፍተቱን የሚሞላበትን ምክረ-ሀሳብ ጥናትን መሰረት በማድረግ ያመነጫል፣ ለመንግስት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱንና

xiinxallote safonni malqummeessa burqissanno; mootimmate shiqishshanno; fajjinirono loosoho hosanna gumaamimma ha’runsitanno.

10. Seeru garinni hidharaasineho (shammaachootaho) agarooshshe assitanno; daddalu udiinnenna owaante tuqishsha qorqortanno.
11. Garimma noo bisinni waagu qorqorsha assinoonninsare safaano daddalu udiinninna owaante loosu aana hosansa illaallissanno.
12. Gadachaano Itophiyu deerri noonsari daddalu udiinninna owaante deeru safaraano wonshansa qorqortanno; qixxaawinonsa deerri woroonni ikkite leeltinori aana qaafo adhitanno.
13. Gobboomunnihu seeraanchu bikku amuraati garunni loosu aana hosamasi illaallissanno.
14. Daddalu handaarinna ogimmate maamarra uurritanno gede jawaachishshanno; uurrinsoonnireno kaajjitanno gede assitanno.
15. Daddalo halashshate ragaanni quchumunna baadiyyete hattono quchummate insa insaneeti quraanyo kaajjitara istiraateeje

ውጤታማነቱን ይከታተላል፡፡

10. በሕግ መሰረት ለሸማቾች ጥበቃ ያደርጋል፣ የንግድ እቃዎችንና አገልግሎቶችን ሥርጭት ይቆጣጠራል፡፡
11. አግባብ ባለው አካል የዋጋ ቁጥጥር የተደረገባቸውን መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች መተግበራቸውን ይቆጣጠራል፡፡
12. አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ይቆጣጠራል፤ ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ ይወስዳል፡፡
13. የሀገሪቱን ሕጋዊ ሥነ-ልክ ሥርዓት በአግባቡ መተግበሩን ይቆጣጠራል፡፡
14. የንግድ የዘርፍና የሙያ ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፡፡
15. ንግድን በማስፋፋት ረገድ የከተማና የገጠር፣ የከተሞች የእርስ በርስ ትስስር እንዲጠናከር ስትራቴጂ ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

qixxeessitanno; loosu aana hosiissanno.

16. Daa”attotenna egensiishshu looso aliidimmatenni massagganno; ha’runsitanno; illaallissanno.
17. Giwirinnu laalchi gumi silanchimma agaranteenna gara dikko gobbate giddoonna gobbaa afidhanno hayyo malte loossanno.
18. Industiretenna ogimmate lifinxe keenate seera loosu aana hosiissanno, silaanchimanna udiinnichu deera hajo la’anonsa bisubba ledo halamatenni tajete woraqatinni buuxissanno.
19. Industirete irko paakeeje qixxeessitanno, qineessitanno, jeefisiissanno, loosu aana hosaseno ha’runsitanno.
20. Industirete qachubba, sheedubba, paarkubbanna kilaasterubba halashshitanno, gatamartanno, hasiisanno qorqorshsha assitanno.
21. Investimentete fajjo noonsa pirojekituwa jeefishsha ha’runsitanno; investimentete fajjo amaddino gadadonna qoosso ayirrisamansanna kakkayishshu hasi’noonni horora hosansa buuxxanno.
22. Qoqqowoho assinanni

16. የኤግዚብሽንና ፕሮሞሽን ስራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።
17. የግብርና ምርት ውጤቶች ጥራታቸው ተጠብቆ ተገቢውን ገበያ በአገር ውስጥና በውጭ እንዲያገኙ ስልት ቀይሶ ይሰራል።
18. የኢንዱስትሪ የሙያ ብቃት መመዘኛ ሕጎችን በስራ ላይ ያውላል፣ የጥራት እና የምርቶች ስታንዳርድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በምስክር ወረቀት ያረጋግጣል፣ የምርት ጥራት ደረጃ እንዲያገኙ ይሰራል።
19. ኢንዱስትሪዎች የድጋፍ ፓኬጅ ያዘጋጃል፣ ያቀናጃል፣ ያስፈጽማል፣ በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል።
20. ኢንዱስትሪ መንደሮች፣ ሼዶች፣ ፓርኮች እና ክላስተሮች እንዲስፋፉ፣ እንዲጠናከሩ ያደርጋል፣ አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል።
21. የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያላቸው ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ይከታተላል፣ በኢንቨስትመንት ፈቃድ የተመለከቱ መብቶችና ግዴታዎች መከበራቸውንና

investimente aana xaaddanno sayikki bissa hi’ra eanna woloota mitiimma la’annonsa bissa ledo waaxamatenni seera agarino garinni tidhantanno gede assitanno.

23. Qoqqowoho investerete dancha investimentete qooxeessa kalaqate dandiissiissanno poolisenna gumulsiisate hayyo qixxeesitanno; garimma noosi bisinni fajiniro loosu aana hosiissanno.
24. Hexxo jeefa gansiisate kaa’litannota wole assootubbano wonshanno.”

**D)** Albi lallawi quwa 14 fidale (J) iima Quchumu Latishshinna minnate Biirora uyineenna keeshino biilloonyinna loosu qeechi konni lallawinni uurritino Quchumu Latishshinna Konistiraakishiinete Biirora saino.

**E)** Albi lallawi quwa 14 fidale (K) rigidante konni woroonni nootenni riqiwantino.

“K) Way, Shiilotenna Inerjete Biiro

1. Qoqqowunnita way jiro gashshitanno.
2. Qoqqowunnita qiletenna aaniidi way jiro bikkunninna

ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ያረጋግጣል፡፡

22. በክልሉ በሚካሄዱ ኢንቨስትመንቶች ላይ የሚከሰቱ የሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነቶችንና ሌሎች ማነቆዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በሕግ አግባብ እንዲፈቱ ያደርጋል፡፡
23. በክልሉ ለባለሀብቶች ምቹ የሆነ የኢንቨስትመንት ከባቢ ለመፍጠር የሚያስችሉ የፖሊሲና የአፈጻጸም እርምጃዎችን ያመነጫል፤ አግባብ ባለው አካል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
24. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡”

**መ)** በነባሩ አዋጅ አንቀጽ 14 ፊደል ተራ (በ) ላይ ለከተማ ልማትና ቤቶች ቢሮ ተሰጥቶ የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ተላልፏል፡፡

**ሠ)** በነባሩ አዋጅ አንቀጽ 14 ፊደል ተራ (ሸ) ተሰርዞ በሚከተለው ፊደል ተራ (ተ) ተተክቷል፡፡

silanchimmatenni baddanno; horote hosanna gara injeessitanno.

3. Way latishshinna gashshooti maanuwallanna deerra qixxeessitanno; woleno way loosi gola illaallissanno.
4. Anganni way shiqisho tittirshi xiinxallo assitanno; gimbaata assitanno.
5. Quchumunna baadiyyennihu xalalu way shiqisho tuqo lophanno gede assitanno; deerra murtanno; tekinikaanchu loosi guunte ha’runsitanno.
6. Baadiyyete way uurrinshuwa gashshooti komitta uurrissanno; seeraancho mannimma fajjoote uytanno; quchumu way owaante uurrinshuwa xintitanno.
7. Qoqqowoho way du’namme farcamaanchimmanna taalashshu way beehaachi qeechi hee’rasi illaallissanno.
8. Way anje noo qoqqowu qarqarubbara winaamu yanna way shiqisho injeessitanno; qarrano hegerimmatenni hunate dandiissanno looso loossanno.
9. Way bisubba burquuqamme gargartanno; qorqortanno; way akeeka gamba assitanno; laaboraatoorete fonqolsha assitanno.

“ተ) የውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ

1. የክልሉን የውሃ ሀብት ያስተዳድራል፡፡
2. የክልሉን የከርሰ ምድርና ገፀ ምድር ውሃ ሀብት በመጠንና በጥራት ይለያል፣ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
3. የውሃ ልማትና አስተዳደር ማኑዋሎችንና ደረጃዎችን ያዘጋጃል እንዲሁም ሌሎች የውሃ ሴክተር ስራዎችን ይቆጣጠራል፡፡
4. የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ዝርዝር ጥናት ያጠናል፣ ግንባታዎችን ያከናውናል፡፡
5. የከተማና ገጠር የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን እንዲያድግ ያደርጋል፣ ደረጃውን ይወስናል፣ የቴክኒካዊ ሥራዎችን አፈፃፀም ይከታተላል፡፡
6. የገጠር መጠጥ ውሃ ተቋማት አስተዳደር ኮሚቴዎችን ያደራጃል ሕጋዊ የሰውነት ፈቃድ ይሰጣል፣ የከተማ ውሃ አገልግሎት ድርጅቶችን ያደራጃል፡፡
7. በክልሉ የውሃ ተፋሰሶች ፍትሐዊና ሚዛናዊ የውሃ

10. Wayinna gorsu latishshi loosira bobbakkanno tequwaraacera, amaalaanoranna ogeeyyera deerra murtanno; loosu fajjoote uytanno; haaroonsitanno; ittissanno; hooltanno.
11. Qoqqowunniha gorsu latishshi tuqo lossate gorsu latishshinna meemiishshu loosi xiinxallonna diizayne looso loossanno; gimbaatu carata qixxeessitanno; loosoho hosiissanno.
12. Laggate du'nama ragi biddonna lolahu gargarooshshi loosi xiinxallo diizaynenna gimbaatu qorqorshi looso loossanno.
13. Qoqqowoho assinanni gorsu konistiraakishiine loosi safaraano qixxeessitanno; loosoho hasiisa massagganno.
14. Gorsu aggaxxo xiinxallo, diizaynenna gimbaati looso massagganno; ha'runsitanno; illaallissanno; dhuka kaajjishshanno.
15. Qoqqowu mootimma widoonni minnoonnita gorsu uurrinshuwa qorobbanno; gatamartanno; gorsu uurrinshuwa qarqaru ogeeyye qajeelshatenni qorobbannonna gashshitanno gede iillishshanno.
16. Federaalete mootimma widoonni qoqqowu giddo

ክፍፍልና ምደባ መኖሩን ይቆጣጠራል፡፡

8. የውሃ ዕጥረት ባለባቸው የክልሉ አካባቢዎች የአስቸኳይ ጊዜ የውሃ አቅርቦት ያመቻቻል፣ ችግሩንም በዘለቄታዊነት ለማስወገድ የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

9. የውሃ አካላት ብክለትን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ የውሃ ናሙና ይሰበስባል፣ የላብራቶሪ ምርመራ ያደርጋል፡፡

10. በውሃና በመስኖ ልማት ስራ ለሚሰማሩ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና ባለሞያዎች ደረጃቸውን ይወስናል፣ የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፡፡

11. የክልሉን የመስኖ ልማት ሽፋን ለማሳደግ የመስኖ ልማትና የማጠንፈፍ ሥራዎች ጥናትና ዲዛይን ያከናውናል፣ የግንባታ ጨረታ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

12. የወንዞች ፍሰት አቅጣጫ መግራት እና የጐርፍ መከላከያ ሥራዎች ጥናት ዲዛይንና ግንባታቁጥጥር ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

hadhanno way latishshi pirojektuwa assootira annimmatenni irko assitanno.

17. Qoqqowu gede loosamanno Shiilo hasatenna latisate loossa aliidimmatenni massaganno; harunsitanno.
18. Qoqqowu gede Inerjete buichonna doorsha halashshate, latisatenna horonsirate amuraate sirsitanno; jeefishshasino harunsitanno.
19. Hexxose jeefisate kaa'liatannota wole loossa loossanno."

**F)** Albi lallawi quwa 14 fidale (L) rigidante konni woroonni nootenni riqiwantino.

"L)Meentu, Wedellunna Dagoomite Hajubba Biiro

1. Meentu, qaaqquullunna wedellu qoossonna horo ayirisiisate qooxeessa hegerrenna millimmo kalqantanno gede assitanno.
2. Heewisamaanonna baqqiima qansichoota kalaqate kaa'liatannota fayyo maate kaajjishshi pirogiraamma halamaano bisubba ledo qinaawatenni suudissanno; loosoho hosanna gumaa'mate

13. በክልሉ የሚካሄዱ የመስኖ ኮንስትራክሽን ሥራዎች መስፈርት ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነቱን ይመራል፡፡
14. የመስኖ አለኝታ ጥናት፣ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ይመራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ አቅም ይገነባል፡፡
15. በክልሉ መንግስት አማካኝነት የተገነቡ የመስኖ ተቋማትን ይንከባከባል፣ ይጠግናል፣ የመስኖ ተቋሞችን በአካባቢው ሙያተኞችን በማሰልጠን እንዲንከባከቡና እንዲያስተዳድሩ ያበቃል፡፡
16. በፌደራሉ መንግስት አማካኝነት በክልሉ ውስጥ ለሚካሄዱ የውሃ ልማት ፕሮጀክቶች ክንውን በባለቤትነት ድጋፍ ያደርጋል፡፡
17. በክልሉ የሚካሄደውን የማዕድን ፍለጋና ልማት ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፡፡
18. በክልሉ የኢነርጂ አማራጮችን የማስፋት፣ የማልማት እና የአጠቃቀም ሥርዓትን ይዘረጋል፣ አተገባበሩንም ይከታተላል፡፡
19. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ

gara ha’runsitanno; illaallissanno.

3. Meentu, qaaqquullunna wedellu ikkito mu’lissannota tittirancho mashalaqqe gamba assitanno; qineessitanno; la’annonsarira baalanko egennantanno gede asitanno.
4. Meentunna wedellu qoqqowoho polotiku, miinjunna dagoomu mittoomu millimmuwa giddo baqqiima ikkite beeqqate dandiissiissanno kaayyo injiitinonsata buuxxanno.
5. Meyatinna wedellu hasattonsanna mitiimmansa garinni qinaabbe qoossonsara sharrantaranna mitiimmuwansa huna dandiitara jawaachishshanno; ikkito injeessitanno.
6. Qoqqowu mootimma bisubbanni qixxaabbanno polisubba, seerubba, latishshu pirogiraammanna pirojektuwa meyatenna wedellu hajo hanqaffanno gede hayyo maltanno; keentanno; gara ikkitino ha’runso assitanno.
7. Qeedhootanna wedella mereersite babbaxxitino uurrinshuwara loosantanno

ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።”

**ረ)** በነባሩ አዋጅ አንቀጽ 14 ፊደል ተራ (ተ) ተሰርዞ በሚከተለው ፊደል ተራ (ቸ) ተተክቷል፡፡

“ቸ) የሴቶች፣ ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ቢሮ

1. የሴቶች፣ የሕፃናትና የወጣቶች መብትና ጥቅሞችን በማስከበር ዙሪያ ግንዛቤና ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡
2. ተወዳዳሪና ንቁ ዜጋን ለማፍራት የሚረዱ የጤናማ ቤተሰብ ግንባታ ፕሮግራሞችን ከአጋር አካላት ጋር በቅንጅት ይቀርጻል፣ ተግባራዊነቱንና ውጤታማነቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
3. የሴቶችን፣ የሕፃናትና የወጣቶችን ሁኔታ የሚያመላክቱ ዝርዝር መረጃዎችን ይሰበስባል ያደራጃል፣ በሚመለከታቸው ሁሉ እንዲታወቁ ያደርጋል፡፡
4. ሴቶችና ወጣቶች በክልሉ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማሕበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችላቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን

loossa ha’runsitanno; buusansiissanno keentanno; taashshaancho qaafo adhitanno; tittirshu biddissunni muramanno.

8. Meentunna qaaqquullu aana iillanno gosoonshanna qohaano rosichu ikkituwanna qonke xiinxallotenni badatenni ba’anno gara injeessitanno; gumulaanchimma ha’runsitanno; hegerre cu’mishiishate looso loossanno.
9. Meentu babbaxxitino mootimmate bisubbara muro aate loosi darguwara qeechamate ikkado illacha tungoonninsata buuxxanno.
10. Woriidi heeshshote deerrira afantanno meenti heeshsho gara woyyeessate kaa’litanno xiinxallo ha’rissanno; pirogiraammanna pirojektuwa qixxeessatenni loosoho hossanno assitanno; liqootenna suuqote owaante afidhanno gara injeessitanno; gumulaanchimma ha’runsitanno.
11. Meentunna wedellu latishshu, danchu gashshootinna dimokiraasete amuraati kaajjishshira baqqiima

ያረጋግጣል፡፡

5. ሴቶችና ወጣቶች እንደ የፍላጎቶቻቸውና እንደ ችግሮቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡
6. በክልሉ መንግስት አካላት የሚያዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ እንዲያካትቱ ስልት ይነድፋል፣ ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፡፡
7. ወጣቱን ማዕከል አድርገው በተለያዩ ድርጅቶች የሚሰሩ ስራዎች ይከታተላል፣ ያስተባብራል ይገመግማል፣ ማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡
8. በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚቃጡ መድሎዎችን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ጥቃቶችን በጥናት በመለየት የሚወገዱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል፣ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ይሰራል፡፡
9. ሴቶች በተለያዩ የመንግስት አካላት በውሳኔ ሰጪ የስራ

beeqqaanonna horaameeyye ikkitara hayyo maltanno; irko assitanno.

12. Meentunna wedellu xintamooshshi dhuka owirsate dandiissiissanno xiinxallo ha’rissanno; qajeelshuwa uytanno; qajeelshu owaante aamantanno assoote injeessanno; buusansiissanno.
13. Amuwu heeshsho woyyaabbannonna qaaqquullu qoossonna adawi agaramanno gara xiinxallitanno; la’annonsa bisubba ledo buusamatenni loosoho hosiisanno.
14. Qoqqowoho meentunna qaaqquulle la’annota gobbanke kalqoomu deerrinni malaatisse adhitino sumiimmuwa gumulaanchimma ha’runsitanno; la’annonsa bisubbara rippoorte shiqishshanno.
15. Dagoomittenna ikonomete qarri giddo noorenna reqecci yitino wogane hegeraamu garinni gatamarate loossa addi addi gutamaano bissa lodo halamatenni jeefisanno.
16. Addi addi handaarinni meessi fajji owaante budu boowiranno hayyo kalaqatenni loossanno.

ቦታዎች ላይ ለመመደብ በቂ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

10. በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴቶችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል፡፡
11. ሴቶችና ወጣቶች በልማት፣ በመልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ላይ ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ስልት ይቀይሳል፣ ድጋፍ ይሰጣል፡፡
12. የሴቶችና የወጣቶች አደረጃጀቶችን አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ስልጠናዎችን ይሰጣል፣ የስልጠና አገልግሎት የሚሰጥበትን አሰራር ያመቻቻል፣ ያስተባብራል፡፡
13. የእናቶች የኑሮ ሁኔታ ስለሚሻሻልበትና የሕፃናት መብትና ደህንነት ስለሚጠበቅበት ሁኔታ ያጠናል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር

17. Bisu muso noonsari, geeru, surrete xisso noonsarinna labbanno addi illacha hasidhanno dagoomu bissa kaa'lonna irko afidhanno mereershubba xintantanno gede hajo la''anonsa bissa ledo waaxotenni loossanno.
18. Hexxo jeefa gansiisate kaa'liatannota wole assootubba assitanno."

**G)** Albi lallawi quwa 14 fidale (N) rigidante konni woroonni nootenni riqiwantino.

"N)Loosu, Dandootenna Interprayizete Latishshi Biiro

1. Qoqqowu giddo looso hasidhanno addinnii wedellunna meyati looso kalaqate hala'ladunni bobbakkanno gede huwanyo kalaqate, qajeelishunni irkisate, loosu base injeesate, liqoote, dikkote xaadooshshi amaalenna woloota kaa'lo afidhanno gede assitanno; injo kalaqqanno.
2. Interpirayzete irko paakeeje qixxeessitanno, qineessitanno, jeefisiissanno, loosu aana hosaseno ha'runsitanno.
3. Manufakcherete laalcho baara

ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

14. በክልሉ ሴቶችንና ሕጻናትን የሚመለከቱ ሀገራችን የፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አፈጻፀም ይከታተላል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ሪፖርት ያቀርባል፡፡
15. ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር የተዳረጉና የተጋለጡ ወገኖች በዘላቂነት የሚቋቋሙበትን ሥራ ከተለያዩ ባለድርሻ አካለት ጋር በመቀናጀት ይተገብራል፡፡
16. በተለያዩ መስኮች የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት ባህል እንዲዳብር ስልት በመቀየስ ይሰራል፡፡
17. የአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የአእምሮ ሕሙማንና መሰል ልዩ ትኩረት ለሚያስፈልጋቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍና እንክብካቤ የሚያገኙባቸው ማዕከላት እንዲደራጁ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡
18. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡"

**ሰ)** በነባሩ አዋጅ አንቀጽ 14 ፊደል ተራ (ኀ) እና (ነ) ተሰርዞ በሚከተለው ፊደል

widira sokkanno Interpirayzoota hajo la’annonsa bisubba ledo halamatenni laalchonsa baara widira sokkanno gede irkissanno.

4. Loosu kaayyo kalaqate amaale mini baalante tantanora uurranno gede assitanno, amaalete minira looso qineesitanno, hasiissanno irko uyitnno.
5. Looso kalaqatenna loosu kaayyo aana xiinxallo assitanno, hajo la’annonsa bisubba shiqishatenni kaajjishiishidhanno, gumulo loosu aana hosase ha’runsitanno.
6. Quchumu sagalete waastinni pirogiraame annimmatenni massagganno, hajo la’annonsa bisubba ledo halamatenni irkissanno, jeefishsha ha’runsitanno, hegeraanchu latishshi ledo waaxo kalaqqanno.
7. Hojji sektere widoonni kalaqantanno seedanna harancho yanna loosu kaayyo jeefishsha ha’runsitanno, irkissanno.
8. Hallanyu handaarira loosiisaanotenna loosaasinete xaadooshshe massagate fultino polisenna seerubba qoqqowu giddo loosu iima hosansa aliidimmatenni harunsitanno.
9. Loosiisaanotenna loosaasinete mereero heeranno lami-xaado

ተራ (ነ) ተተክቷል፡፡

“ነ) የሥራ፣ የክህሎትና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ

1. የክልሉ ሥራ ፈላጊዎች በተለይም ለወጣቶች እና ለሴቶች በስራ ፈጠራ ላይ በስፋት እንዲሰማሩ ግንዛቤ ይፈጥራል፣ የስልጠና ድጋፍ፣ የመስሪያ ቦታ፣ ብድር፣ ገበያ ትስስር ምክር እና ሌሎች ድጋፎች እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ያመቻቻል፡፡
2. የኢንተርኘራይዞች የድጋፍ ፓኬጅ ያዘጋጃል፣ ያቀናጃል፣ ያስፈጽማል፣ በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፡፡
3. የማኑፋክቸሪንግ ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ ላይ ለተሰማሩ ኢንተርኘራይዞች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ምርታቸውን ለውጭ ሀገር እንዲያቀርቡ ያግዛል፡፡
4. የስራ ዕድል ፈጠራ ምክር ቤት በሁሉም ደረጃ እንዲቋቋም ያደርጋል፣ የምክር ቤቱን ስራ ያደራጃል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡
5. የስራ ፈጠራ እና የስራ እድል ላይ ጥናት ያደርጋል፣ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ

hattono loosiisannote, loosaasinetenna mootimmate mereero heeranno sasi-xaado kaajishshanno loossa loosanno.

10. Loosu yekeero qaroomi'no garinni gumulo afidhanno gede irkisanno amuraatubba sirsitanno, jeefishshansano harunsitanno.
11. Seeru garinni fajjo afidhe qoqqowu giddo addi addi loosu handaarira bobbakkino baara widi qansoota borreessitanno, harunsitanno, loosu fajjonsa haaroo'mase buuxanno.
12. Addi addi mootimmate uurrinshshuwa giddonna mootimmatenni loosantanno addi addi pirojektubba widoonni kalaqantanno loosu kaayyo jeefishsha ha'runsitanno.
13. Qoqqowoho ikkitannota tekiniketenna ogimmate qajeelshi pirogiraamma gobboomu deerransa agadhite ha'ransa buuxxanno.
14. Deerrase agadhitino safoniti boodillaananna mereerima tekiniketenna ogimmate rosi qajeelshi kaarkuleeme qixxaabanno gede assitanno; ha'runsitanno; irkissanno.
15. Qoqqowoho industiretenna investimentete millimmo

ሲጸድቅ ስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፡፡

6. የከተማ ምግብ ዋስትና ፕሮግራምን በባለቤትነት ያስተባብራል፣ ከሚመለከታቸውም አካላት ጋር በመቀናጀት ይደግፋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ ዘላቂነት ካለው የልማት ተግባር ጋርም ያስተሳስራል፡፡
7. በግሉ ሴክተር አማካይነት ሊፈጠሩ ስለሚገባቸው ዘላቂና ጊዜያዊ የሥራ ዕድሎች አተገባበር ይከታተላል፤ ይደግፋል፡፡
8. የግሉ ሴክተር የአሰሪና የሠራተኛ ግንኙነት ለመምራት የወጡ ፖሊሲዎች እና የሕግ ማዕቀፎች በክልሉ ተግባራዊ መሆናቸውን በበላይነት ይከታተላል፡፡
9. በአሰሪና በሰራተኞች መካከል ያለውን የሁለትዮሽ ግንኙነት እንዲሁም በአሰሪ፣ በሠራተኛና በመንግሥት መካከል ያለውን የሦስትዮሽ ግንኙነትን የማጠናከር ተግባራትን ያከናውናል፡፡
10. የሥራ ክርክሮች በተፋጠነ መንገድ መፍትሄ እንዲያገኙ የሚያስችሉ አሰራሮችን ይዘረጋል፤ ተግባራዊነታቸውንም

irkissannota safonita boodillaananna mereerimu deerri tekinikete ogimma qajeelshu uurrinshuwa uurrissanno; halashshitanno; gashshitanno.

16. Tekiniketenna ogimmate rosinna qajeelshi kolleejuwanna hakko handaarira bobbakkannore wole qajeelshu uurrinshuwara balaxi-afamooshshunna afamooshshu fajjoote uytanno; haaroonsitanno; deerru woroonni higge leelturo fajjootensa hooltanno.
17. Rosunna qajeelshunniha ogimmate ikkadimma buuxishshi amuraate qixxeessitanno; jeefishshasi ha’runsitanno; illaallissanno.
18. Konni handaarira hojji dureeyyenna mootimmaweelo uurrinsha beeqqitanno gara injeessitanno; jawaachishshanno; hasiissanno irko assitanno.
19. Qoqqowunnita tekiniketenna ogimmate rosinna qajeelshi istiraateeje qixxeessitanno; fajjiniro jeefissanno; jeefisiissanno.
20. Qoqqqowoho taalchunna farcamaanchu tekiniketenna

ይከታተላል፡፡

11. ሕጋዊ የሥራ ፈቃድ አግኝተዉ በክልሉ በተለያዩ የሥራ መስኮች የሚሰሩ የዉጭ ዜጎችን ይመዘግባል፣ ይከታተላል፣ የሥራ ፈቃዳቸዉ መታደሱን ያረጋግጣል፡፡
12. በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ውስጥ እና በመንግስት በሚሰሩ ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች አማካይነት የሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች አፈጻጸም ይከታተላል፡፡
13. በክልሉ የሚከናወኑ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ፕሮግራሞች አገር አቀፍ ደረጃቸውን ጠብቀው መካሄዳቸውን ያረጋግጣል፡፡
14. ደረጃውን የጠበቀ መሰረታዊ መለስተኛና መካከለኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ-ትምህርት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፡፡
15. በክልሉ የኢንዱስትሪና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴውን የሚያግዙ መሰረታዊ መለስተኛና መካከለኛ ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማትን ያቋቁማል፣ ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፡፡
16. ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆችና በዘርፉ ለሚሰማሩ ሌሎች ማሰልጠኛ

ogimmate qajeelshi tuqishshi hee’ranno gede assitanno.

21. Dikkote hasatto mereersinoha rosaminonna rosaminokki qajeelshi pirogiraame roso qixxeessitanno; loosu aana hossanno gede assitanno; karikuleme qixxaabbanno raga leellishshanno.
22. Tekiniketenna ogimmate qajeelshi mereershuwa albillicho fulonsa uminsanni wonshi’ra dandiissitannota eo lossate raga maltanno.
23. Tekiniketenna ogimmate qajeelshi uurrinshuwa gutoomunni qajeelsha uytanno assooti biddissa fushshitanno; jeefishshaho irkissanno; ha’runsitanno.
24. Qoqqowunnita sayinsetenna tekinoloojete hasatto baddanno, hajo la’annonsa bisubba ledo malamatenni hasatto wonshinanni gara injeessitanno.
25. Hajo la’annonsa bisubba ledo halamatenni qoqqowu giddo tekinoloojete paarke uurritanno gede assitanno.
26. Hexxose loosu aana hosiisate hasiissanno wole hajubba jeefisiissanno.”

ተቋማት የቅድመ-ዕውቅናና ዕውቅና ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል ከደረጃው በታች ሆነው ሲገኙ ፈቃዳቸውን ይሰርዛል፡፡

17. የትምህርትና ሥልጠና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ያዘጋጃል፣ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
18. በዘርፉ የግል ባለሀብቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚሳተፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ያበረታታል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡
19. የክልሉን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂ ያዘጋጃል ሲፈቀድም ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፡፡
20. በክልሉ ተመጣጣኝ እና ፍትሃዊ የቴክኒክና ሞያ ስልጠና ሽፋን እንዲኖር ያደርጋል፡፡
21. የገበያ ፍላጎት መሰረት ያደረገ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆነ ስልጠና መርሃ-ግብር ትምህርት ያዘጋጃል፣ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ስርዓተ ትምህርት የሚዘጋጅበት አቅጣጫ ይነድፋል፡፡
22. የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከላት ወደ ፊት ወጪያቸውን በራሳቸው መሸፈን የሚያስችል የገቢ ማሳደግያ

**H)** Albi lallawi quwa 14 fidale (Q) iima Mootimmate Kominikeeshine Biirora uynonni biilloonyinna loosu qeechi konni lallawinni uurritino Pirees Sekireteriyatete saino.

**I)** Albi lallawi quwa 14 fidale (R) rigidante konni woroonni nootenni riqiwantino.

"R) Pilaanetenna Latishshu Biiro

1. Qoqqowunnita seeda, mereerimanna harancho yanna mixo qixxeessitanno, jeefishsha ha'runsitanno, keentanno, rippoorte qixxeessatenni hajo la'annonsa bisubbara shiqishshanno.
2. Maakiro Ikkonoometenna fiizikaale hajubba mami-geeshsha qixxeessitanno, jeefisiisaanote amaale minira shiqishshe kaajjishiishshanno.
3. Qoqqowu mootimma kappitaale pirojektubba hornyi xiinxallo assitanno, keentanno, kaajjishiishshanno.
4. Qoqqowu gashshootu taqqubba dirunnita jajju beehaachi afi'ri-mala qixxeessitanno, qoqqowu amaale minira shiqishatenni kaajjishiishshanno.
5. Qoqqowunnita kappitaale pirojektubba jeefishsha

የአፈፃፀም አቅጣጫ ይነድፋል፡፡

23. የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከላት በሽርክና ስልጠና የሚሰጡበትን የአሰራር መመሪያ ያወጣል፣ ለአፈፃፀሙ ይደግፋል፣ ይከታተላል፡፡
24. የክልሉን የሳይንስና የቴክኖሎጂ ፍላጎት ይለያል፣ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመመካከር ፍላጎቱ የሚሟላበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
25. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ የቴክኖሎጂ ፓርኮች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፡፡
26. ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡"

**ሸ)** በነባሩ አዋጅ አንቀጽ 14 ፊደል ተራ (አ) ለመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ ተሰጥቶ የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ መሰረት ለተቋቋመው ፕሬስ ሴክሬታሪያት ተላልፏል፡፡

**ቀ)** በነባሩ አዋጅ አንቀጽ 14 ፊደል ተራ (ከ) ተሰርዞ በሚከተለው ፊደል ተራ (ከ) ተተክቷል፡፡

"ከ) ፕላንና ልማት ቢሮ

1. የክልሉን የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅድ ያዘጋጃል፤

ha’runsatenni keentanno, yannitte rippoorte qixxeessite hasiissanno bisubbara shiqishshanno.

6. Maakiro ikkonoomete polise jeefishshi xiinxallo ha’rissanno.
7. Qoqqowunnita latishshu xe’nenna latate dhuki xiinxallo assitanno.
8. Qoqqowinnita dagoomittenna miinju akati xiinxallo assitanno.
9. Qoqqowunnita mereerima yanna maakiro ikkonoometenna fiizikaale hajo mami-geeshsha qixxeessitanno, kaajjishiishshanno.
10. Qoqqowunita diru jiro geeshsha hedate taje qixxeessitanno፣ qoqqowu jeefisiisaanote amaale minira shiqishatenni kaajjishiishshanno.
11. Qoqqowunnita miinju, dagoomittenna baattote ofolla taje gamba assitanno, maarekkitanno, tittirsha qixxeessatenni horonsi’raanote tuqissanno.
12. Qoqqowunnita dagoomittenna miinju latishshi beehaachenna baattote ofolla xawissanno atilaasenna kaarta qixxeessitanno.
13. Qoqqowu mootimma uurrinshuwa loosinsa qeechinni qixxeessitanno istatistiksete taje gamba assitanno, maarekkitanno, tittirsha assatenni horonsi’raanote iillitanno gede assitanno, hattono deerrasinna

አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤ ይገመግማል፤ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፡፡

2. የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቅፍ ያዘጋጃል፤ ለመስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፡፡
3. የክልሉን መንግሥት የካፒታል ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት ያካሂዳል፤ ይገመግማል፤ ያስፀድቃል፡፡
4. በክልሉ ለታችኛው የአስተዳደር ዕርከን ዓመታዊ የሀብት ማከፋፈያ ቀመር ያዘጋጃል፣ ለክልሉ ምክር ቤት እንዲጸድቅ ያቀርባል፡፡
5. የክልሉን የካፒታል ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፤ ወቅታዊ ሪፖርት በማዘጋጀት አግባብነት ላላቸው አካላት ያቀርባል፡፡
6. የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ አፈፃፀም ጥናት ያካሂዳል፡፡
7. የክልሉን የልማት ክፍተት እና የመልማት አቅም ጥናት ያደርጋል፡፡
8. የክልሉን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ገፅታ ጥናት ያደርጋል፡፡
9. የክልሉን የመካከለኛ ጊዜ የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ

silaanchimmasi agadhino garinni qixaawanno gede irko assitanno, ha’runsatenna qorqorate looso loosanno, tajete qorqorshi gumi kaiminni hasiissanno woyyeessate qaafo adhitanno.

14. Qoqqowunnita tajete foonqe taashshate xiinxallonna buuxote looso loossanno.
15. Qoqqowunnita istatistiksete taje amanyoote yannisate mootimmate uurrinshuwara irko uytanno, looso qineessitanno, massagganno.
16. Dagaallo hajubba latishshu mixo giddo amade jeefisa lainohunni mootimmannitinna mootimmaweelo uurrinshuwa massagganno.
17. Dagaallo hajubba lainohunni dagoomunna gashshootu bisubbara huwanyo kaajjishate kaa’litanno rosunna kakayishshu looso loossanno.
18. Dagaallo latishshu hajubba laainohunni xiinxallotenna buuxote looso loossanno.
19. Qoqqowunnita dagaallo polise loosu aana hosiisate, jeefisate kaa’litanno biddissubbanna maanuwalla fushshitanno.
20. Gashshootu taqqara heedhanno dagaallote amaale minna kaajjishatenna gutamaano bisubba qineessatenni ontu dirita

ያዘጋጃል፤ ያስፀድቃል፡፡

10. የክልሉን ዓመታዊ የሀብት ግመታ ሰነድ ያዘጋጃል፤ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በማቅረብ ያስፀድቃል፡፡
11. የክልሉን የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና መልክአ ምድራዊ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ያደራጃል፤ ትንተና በማድረግ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፡፡
12. የክልሉን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ልማት ስርጭትንና የመልክዓ ምድራዊ ገፅታን የሚያሳይ አትላስና ካርታ ያዘጋጃል፡፡
13. የክልሉ መንግሥት መስሪያ ቤቶች በሥራቸው ኃላፊነት የሚያመነጩትን ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተንና ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆን የማድረግ እንዲሁም ስታንዳርዱንና ጥራቱን ጠብቆ እንዲዘጋጅ ድጋፍ፣ ክትትል እና ኦዲት ያደርጋል፣ በመረጃዎች ኦዲት ግኝት መሠረት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡
14. የክልሉን የመረጃ ክፍተት ለማሟላት የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያከናውናል፡፡
15. የክልሉን የስታቲስቲክስ መረጃ ሥርዓት በማዘመን

dagaallote pirogiraame qixxeessitanno, dagaallote amaale minira shiqishshe kaajjishiishshanno, loosu aana hosase ha'runsitanno, keennanni raga wortanno.

21. Mixotenna pirojekte qixxeessa, ha'runsanna keena lainohunni dhuka kaajjishate looso loossanno.
22. La'annonsa qoqqowu mootimma bisubba ledo buusamatenni seeda, mereerimanna harancho yannanni loosu aana hossanno waacantino pirojektuwanna pirogiraamma qixxaabbanno gede assitanno; fajjanturono loosu aana hosansa ha'runsitanno.
23. Maakirote miinji xiinxallo ha'rissanno; xiinxallote guma mootimmate shiqishshanno.
24. Hexxose loosu aana hosiisate hasiissanno wole hajubba jeefisiissanno."

**J)** Albi lallawi quwa 14 fidale (R) aante konni woroonni noo haaro woro fidale (S) ikkite ledantino.

"S) Saadate Jiro Latishshi Biiro

1. Saadate jiro (mini saada, diida, qulxumenna wkl.) latishshi handaara halashshate

ለመንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ድጋፍ ይሰጣል፤ ሥራውን ያስተባብራል፤ ይመራል፡፡

16. የሥነ-ህዝብ ጉዳዮችን በልማት ዕቅድ አካቶ ከመተግበር አኳያ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ያስተባብራል፡፡
17. በሥነ-ህዝብ ጉዳዮች የማህበረሰቡንና አመራር አካላትን ግንዛቤ ለማጎልበት የሚያስችሉ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራዎችን ያካሂዳል፡፡
18. የሥነ-ህዝብና ልማት ጉዳዮችን በተመለከተ የጥናትና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል፡፡
19. በክልሉ የስነ-ህዝብ ፖሊሲ ለመተግበር፣ለአፈፃፀሙ የሚረዱ መመሪያዎች እና ማንዋሎች ያወጣል፡፡
20. በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙትን የሥነ-ህዝብ ም/ቤቶችን በማጠናከርና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር የአምስት ዓመት የሥነ-ህዝብ ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ለሥነ-ህዝብ ም/ቤቱ በማቅረብ ያፀድቃል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ይገመግማል አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡
21. በዕቅድና ፕሮጀክቶች ዝግጅት

kaa'litanno polise, istraateeje, seera qixxeessitanno, fajjinanni woyte loosu aana hosase ha'runsitanno, qorqortanno, jeefisanno.

2. Saadate jiro latishshi ekistenshiine paakeejje qixxeessatenni jeefissanno, jeefisiissanno, ha'runsitanno, ekistenshiinete ha'rinshono xiinxallotenni woyyaabbanno gede assitanno.
3. Qoqqowu giddo afamanno saadate sircho latishshu laayyonni baddanno, istiraatejike mixo qixxeessitanno, loosu aana hosiissanno, ha'runsitanno, qorqortanno.
4. Qoqqowu giddo laalichimasenninna xibba gargadhate dhukinni afantinore saadate sircho agarate haja la'anonsa bissa ledo halante loossanno.
5. Hegeraame ikkitino saadate sagale shiqo buuxisiisate woyyaabbino saadate sagale latishshi loossa loossanno, kalaqamu jiro latishshinna agarooshshi ledo qinaawe lattanno gede assitanno, qineessitanno.
6. Saadate laalchonna laalchimma

ክትትልና ግምገማ ዙሪያ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

22. ከሚመለከታቸው የክልሉ የመንግስት አካላት በመተባበር በረጅም፣ በመካከለኛ እና በአጭር ጊዜ የሚተገበሩ የተቀናጁ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ከተፈቀዱ በኋላም ተግባራዊ መሆናቸው ይከታተላል፡፡
23. የማክሮ ኢኮኖሚ ጥናት ያካሀዳል፣ የጥናቱ ውጤት ለመንግስት ያቀርባል፡፡
24. ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡"

**በ)** በነባሩ አዋጅ አንቀጽ 14 ፊደል ተራ (ከ) ቀጥሎ ከዚህ በታች የተመለከተው አዲስ ድንጋጌ ፊደል ተራ (ኸ) ሆኖ ተጨምሯል፡፡

"ኸ) የእንስሳት ሀብት ልማት ቢሮ

1. የእንስሳት ሀብት (የቤት እንስሳት፣ ንብ፣ ዓሣና ወዘተ.) ልማት ዘርፍን ለማስፋፋት የሚረዳ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ህጎችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀዱም በሥራ ላይ መዋላቸዉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያስፈፀማል፡፡

lossinanni gibiaate shiqo injeessitanno, hala'litanno gede assitanno.

7. Qoqqowu deerrinni saadate xibbi qorqorshi isitiraateeje qixxeessitanno, jeefisiissanno, hasiise leelliro qaafo adhanno.
8. Gargarooshshe safo assino saadate fayyimma owaante uyitanno, saadate xibbi buuxo assanna qorqorshu loossa loossanno.
9. Keeraanchimmasinna isilanchimmasi agarantino maalinna saadate laalichi dagate shiqanno gede saada gorrinanni baycho maalu buuxo assitanno, deerra agarino saada gorrinanni mini baadiyyetenna quchummate minamanno gede ha'runsonna irko assanno.
10. Eeliidi tantanora saada xagisatenna kilinikete owaante uyitanno.
11. Saadatenna saadate laalichi latishshinna daddali, saadate xagishshi owaante aate bobbakkinorira fultinonna fultanno dandoote buuxishshi bikki garinni dandoote keeno assitanno, taje uyitanno, haaronsitanno, qinaambetenni ha'runsonna qorqorsha assitanno.

2. የእንስሳት ሀብት ልማት ኤክስቴንሽን ፓኬጆችን በማዘጋጀት ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣ ይከታተላል፣ የኤክስቴንሽን ሥረዓቱን በማጥናት እንዲሻሻል ያደርጋል።
3. በክልሉ ዉስጥ የሚገኙ የእንስሳት ዝሪያዎችን በልማት ቀጠናዎች ይለያል፣ ስትራቴጂክ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ይተገብራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።
4. በክልሉ ዉስጥ ምርታማነታቸዉንና በሽታን በመቋቋም የታወቁ የእንስሳት ዝሪያዎችን ለመጠበቅ ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ ጋር በቅንጅት ይሰራል።
5. አስተማማኝ የእንስሳት መኖ አቅርቦትን ለማረጋገጥ የተሻሻለ የመኖ ልማት ሥራዎችን ያከናውናል፣ ከተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ጋር አቀናጅቶ እንዲለማ ያደርጋል፤ ያስተባብራል።
6. የእንስሳት ምርትና ምርታማነት ማሳደጊያ ግብዓት አቅርቦት ያመቻቻል፣ እንዲባዙም ያደርጋል።
7. ክልል አቀፍ የእንስሳት በሽታ ቁጥጥር ስትራቴጂ ይነድፋል፣ ያስፈፅማል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ

12. Qoqqowu giddo saadate daddali doogga baddanno, fooliishshote mereershi uurranno gede assitanno, kowaarantinenna qorqorshu mereershubba tantanatenni qoqqowu giddo, qoqqowunni fultannonna e’anno saadda qorqortanno, multanno qoqqowubbanna federaalete mootimma bissa ledo halamatenni loossanno.
13. Saadate laalchonna laalchimma lossinanninna woyyeessinanni gibiatta shiqo injeessitanno, qineesitanno.
14. Saadate Latishshiranna agarooshshira hasiissanno safote latishshuwa uurritannonna hala’litanno gede assitanno, aliidimmatenni massaganno, gashshitanno.
15. Saadate jiro latishshinni bobbakkinori loosidhenna allaa’lite galtinoriranna dureeyyete isilanchonna deerrase agadhitino saadanna saadate laalicho shiqishshanno gedenna owaante uytanno gede dhuka kaajjishate loosonna ogimmate irko assitanno.
16. Hajo la’annonsa mootimmatenna mootimmaame ikkitinokki bissa ledo halamatenni loossanno.

እርምጃ ይወስዳል፡፡

8. መከላከልን መሰረት ያደረገ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ይሰጣል፣ የእንስሳት በሽታዎች ምርመራ፤ አሰሳና ቁጥጥር ሥራዎችን ያካሂዳል፡፡
9. ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ የሥጋና የእንስሳት ተዋፅኦዎች ለህብረተሰቡ እንዲቀርቡ በቄራዎች የሥጋ ምርመራ እንዲካሄድ ያደርጋል፣ ደረጃቸዉን የጠበቁ ቄራዎች በገጠርና በከተሞች እንዲገነቡ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡
10. በተዋረድ ባሉ አደረጃጀቶች የእንስሳት ህክምና ክሊኒክ አገልግሎት ይሰጣል፡፡
11. ለእንስሳትና እንስሳት ተዋጽኦ ልማትና ንግድ ለእንስሳት ህክምናና ክልኒክ አገልግሎት ለሚሰማሩ አካላት በወጡና በሚወጡ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች መሰረት የብቃት ምዘና ያደርጋል፣ ማስረጃ ይሰጣል፣ በቅንጅት ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
12. በክልሉ ዉስጥ የእንስሳት ንግድ የጉዞ መስመሮችን ይለያል፣ ማረፊያ ጣቢያዎች እንዲቋቋሙ ያደረጋል፣ የኳራንታይንና የፍተሻ ማዕከላትን በማደራጀት በክልሉ

17. Qoqqowoho heedhanno saadate jiro latishshi taje yannilaancho doogonni gamba assitanno, maarekkitanno, fatilsitanno, horote aana hosanna gede assitanno.
18. Saadate jiro latishshinni leelitanno dancha rosichuwa gamba assite maarekkatenni wole qooxeessuwara hala’litanno gede assitanno.
19. Hexxose loosu aana hosiisate hasiissanno wole hajubba jeefisiissanno.”

**3. Qoossonna Gadacho Saysa**

Albi lallawi quwa 9 nna 14 garinni uurrite loossanni keeshshitino jeefisiisaanonna hundaano uurrinshubbanni kalaqantino qoossonna gadacho woyyaawino lallawi garinni uurritino labbanno uurrinshubba woy biilloonyunna loosu qeechi ha’rino uurrinshubbara sa’ino.

**4. Lallawu Loosu Iima Hosanno Yanna**

Kuni lallawi Wocawaaro 20/2014 M.D hanafe loosu iima hosannoha ikkanno.

**Hawaasa, Wocawaaro 20, 2014 M.D**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidaanticha**

ዉስጥ፤ ከክልሉ የሚወጡና የሚገቡ እንስሳትን ይቆጣጠራል፣ ከአጎራባች ክልሎችና ከፌዴራል መንግስት አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

13. የእንስሳት ምርትና ምርታማነት ማሳደጊያና ማሻሻያ ግብዓቶች አቅርቦት ያመቻቻል፣ ያስተባብራል፡፡
14. የእንስሳት ሀብት ልማትና ጥበቃ የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶች እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ ያደርጋል፤ በበላይነት ይመራል፤ ያስተዳድራል፡፡
15. በእንስሳት ሀብት ልማት ለተሰማሩ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮችና ባለሀብቶች ጥራትና ደረጃዉን የጠበቀ እንስሳትና የእንስሳት ተዋፅኦ እንዲያቀርቡና አገልግሎት እንዲሰጡ የአቅም ግንባታ ሥራና የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፡፡
16. ከሚመለከታቸዉ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡
17. የክልሉን የእንስሳት ሀብት ልማት መረጃ በዘመናዊ መልኩ ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ጥቅም ላይ እንዲዉል ያደርጋል፡፡
18. በእንስሳት ሀብት ልማት ላይ

የሚገኙ መልካም ተሞክሮዎችን በመቀመርና ከሌሎች አካባቢዎች ከሚገኙ ምርጥ ተሞክሮዎች በማጣጣም እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

19. ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።"

**3. መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ**

በነባሩ አዋጅ አንቀጽ 9 እና 14 ተቋቁመው ሲሰሩ በነበሩ አስፈጻሚ እና ተጠሪ ተቋማት ተፈጥረው የነበሩ መብትና ግዴታዎች በማሻሻያ አዋጁ መሰረት ወደ ተቋቋሙ ትይዩ ተቋማት ወይም ሥልጣንና ተግባራቸው ወደ የሄዱበት ተላልፈዋል።

**4. አዋጁ ሥራ ላይ ስለ ሚውልበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከመስከረም ፳ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ሥራ ላይ የሚውል ይሆናል።

**ሀዋሳ፣ መስከረም ፳ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም**

**ደስታ ሌዳሞ**
**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር**